የወ/መ/ቁጥር 164649

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ 1 ኛ ወ/ሪት ሔለን አለማየሁ ገላን - ቀረበች

2 ኛ ወ/ሪት ጽጌረዳ አለማየሁ ገላን - ቀረበች

3 ኛ ወሪት መሰረት አለማየሁ ገላን - ቀረበች

4 ኛ ወ/ሪት ትዕግስት አለማየሁ ገላን - ቀረበች

5 ኛ ወ/ሪት ሰላም አለማየሁ ገላን - ቀረበች

6 ኛ ወ/ሪት ስህን አለማየሁ ገላን - ቀረበች

7 ኛ ወ/ሪት ነፃነት አለማየሁ ገላን - ቀረበች

8 ኛ ወ/ሮ ብርቱካን አለማየሁ ገላን - ተቋረጠ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተግፈ የተሻሻለ የወንጀል ክስ አቤቱታ በአንደኛው ክስ ሁሉም ተከሳሾች በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 690(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዩ ቦታው ዕድገት አካባቢ ንብረትነቱ የግል ተበዳዮች 1 ኛ) ወ/ሮ ልደት ደመላሽ፤ 2 ኛ) አቶ ስንሻው ደመላሽ፤ 3 ኛ) ሰላማዊት ደመላሽ፤ 4 ኛ) ያፈት ደመላሽ፤ 5 ኛ) ቤተልሔም ደመላሽ የሆነውን ለጊዜው ካልተያዘ ተጠርጣሪ ጋር በመሆን ሁከት በመፍጠር፤ ድንጋይ በመወርወር የመስኮት መስታውት የሰበሩ በመሆኑና የግቢ የብረት ብር እንዲጣመም ያደረጉ በመሆኑ በፈፀሙት በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሰዋል፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ አንደኛ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 27(1) እና 605(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ከላይ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ በአንደኛው ክስ ላይ በተጠቀሱት የግል ተበዳዮች ከሚኖሩበት የመኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ለመግባት በአንድ እጇ ድንጋይ፤ በሌላኛው እጇ ደግሞ ቢላዋ በመያዝ እንዲሁም እንጨርሳችኋለን፤ አትኖሩም፤ ሰፈራችን ካልለቀቃችሁልን ታልቃላችሁ በማለት ዛቻ በመፈፀም በአጥር ላይ ዘላ ለመግባት ስትሞክር የተያዘች በመሆኑ በፈፀመችው የግል ቤቶችን ወይም የተከለከሉ ቦታዎች መድፈር ሙከራ ወንጀል ተከሳለች በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ

ለተከሳሾች (ከ1ኛ-7ኛ ለተጠቀሱት) ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፀ/ሕግ ከግል ተበዳዮች ቤተሰቦች አምስት፤ በአካባቢው ከነበሩ ጎረቤቶች ደግሞ ሁለት በድምሩ ሰባት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በሰጡት ምስክርትም እነዚህ ሰባት ተከሳሾች እና ሌሎች እዚህ ችሎት ያልቀረቡ ግለሰቦች በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ የግል ተበዳዮችን መኖሪያ ቤትና በር በተደጋጋሚ ጊዜ ድንጋይ እየወረወሩና እየጮሁ ሁከት ሲፈጥሩ እንደነበር፤ ወደ ግቢው ይወረውሩት የነበረው ድንጋይም የቤቱን መስታውት እንደሰበረው፤ አንደኛ ተከሳሽ በዕለቱ ገጀራ ነገር ይዛ ወደ ግቢው በግንቡ በኩል ለመግባት ስትሞክር ጎረቤት ነን ብለው ቀርበው የመሰከሩት ምስክሮችና የራሷ የተከሳሽ ወንድም ጭምር ጎትተው አውርደው ወደ ቤቷ እንደወሰዷት፤ በዕለቱ አጠቃላይ ተከሳሾች ለገላጋይ እንኳ አስቸግረው በኋለ የፖሊስ ኃይል መጥቶ ወደ ጣቢያ ሲወስዳቸው ነገሩ ሊበርድ እንደቻለ ምስክሮቹ አንድ በአንድ ያስረዱ በመሆናቸው፤ ፍ/ቤቱም ይህ የተከሳሾች ድርጊት በሕግ ክልከላ የተደረገበት ስለሆነ ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾች በአንደኛው ክስ፤ አንደኛ ተከሳሽ ደግሞ በተጨማሪ በሁለተኛው ክስ መሰረት እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾችም እንከላከላለን ብለው በጋራ ሦስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡት በወቅቱ ፀቡ በአንደኛ ተከሳሽ እና በግል ተበዳዮች ቤተሰብ አባለት የሆኑት ያፈት ደመላሽ እና ስንሻው ደመላሽ መካከል እንደነበር፤ በዚህም ምክንያት አንደኛ ተከሳሽን የደበደባት መሆኑን፤ ከዚያም በኋላ የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ወደ ተከሳሽ መኖሪያ ቤት ድንጋይ በመወርወር በቦታው ቆሞ የነበረ መኪና መስታውት መሰበሩን፤ ከአንደኛ ተከሳሽ እና ከአንደኛ የመከላከያ ምስክር(አምሳለ አለማየሁ) ሌላ ሌሎች ተከሳሾች ውጭ አለመኖራቸውን እናስረዳለን በማለት አስመዝግበው ሦስቱም የመከላከያ ምስክሮችም መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሾች በፀ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮች አንደኛ እና ሦስተኛ እህትና ወንድም ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ አባታቸው ናቸው። አባትና ወንድም ወደ ቦታው የመጡት ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ስልክ ተደውሎላቸው ስለሆነ ከዚያ በፊት ተከሳሾች የፈፀሙትን የወንጀል ድርጊት ለማየት ስለማይችሉ ተከሳሾች በክሱ ላይ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት አልፈፀሙም በማለት ሊያስተባብሉላቸው አይችሉም። የተከሳሾች እህት የሆነችው ምስክርም በወቅቱ ነበርኩ ብትልም፤ የትኞቹ ተከሳሾች ቤት ውስጥ፤ የትኞቹ ደግሞ ከቤት ውጭ እንደነበሩ በግልፅ ለማስረዳት አልቻለችም። ከዚህም ሌላ የተከሳሾችም ሆነ የግል ተበዳዮች ዘመድ ያልሆኑትና ገለልተኛ ጎረቤቶች በሰጡት ምስክርነት በግልፅ ተከሳሾች በወቅቱ በክሱ ላይ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀማቸውን ያስረዱ ሲሆን፤ ተከሳሾች ግን እነዚህ ገለልተኛ የሆኑ ምስክሮች የሆኑት የሰጡትን ቃል የሚያስተባብል ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም። በመሆኑም ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ያሉት ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 690(1) ስር፤ አንደኛ ተከሳሽ በተጨማሪ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 27(1) እና 605(ሀ) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

የቅጣት አስተያየት

ዐ/ሕግ፡ በሁሉም ተከሳሾች ላይ የምናቀርበው የቅጣት ማክበጃ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(መ) ላይ የተመለከተው ሲሆን፤ ይሄውም ድርጊቱን የፈፀሙት በጋራ ስለሆነ ከብዶ እንዲወሰን፤ በሌላ በኩል አንደኛ ተከሳሽ በሁለት ድርጊቶች ጥፋተኛ የተባለች ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 መሰረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ። በተጨማሪም ሁለተኛው ጥፋት ሙከራ ስለሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 20 መሰረት ፍ/ቤቱ ቅጣት ሲወሰን ሁለት እርከን ዝቅ በማለት እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

ተከሳሾች፡

1ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 20 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ ሥራዬ መምህር ነኝ፤ የትምህርት ደረጃዬ 10+3 ነው፤ የወር ገቢዬ ብር 973.00(ዘጠኝ መቶ ሰባ ሦስት) ብር ነው፤ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ተማሪ ነኝ በማለት አመለከተች።

2ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 25 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የትምህርት ደረጃዬ 12ኛ ክፍል ነው፤ ሥራ የለኝም፤ ከቤተሰብ ጋር ነው የምኖረው በማለት አለች።

3ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 26 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ ሥራዬ መምህርነት ነው፤ የወር ደመወዜ ብር 500.00(አምስት መቶ ብር) ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 12 1 ነው፤ በአሁኑ ሰዓት ቪዲዬግራፊ እማራለሁ በማለት አመለከተች።

4ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 35 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የትምህርት ደራጃዬ 12ኛ ክፍል ነው፤ ሥራ የለኝም፤ ከቤተሰብ ጋር እኖራለሁ አለች።

5ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 17 ዓመት ነው፤ ሥራዬ ተማሪ ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ አሁን ፈተና ጨርሼ ከቤተሰብ ጋር እየኖርኩ ነው አለች።

6ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 19 ዓመት ነው፤ ሥራዬ ተማሪ ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የምማረውም 10+3 ነው በማለት ገለጸች።

7ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 24 ዓመት ነው፤ ሥራዬ መምህርነት ነው፤ የትምህርት

ደረጃዬ ዲፕሎማ ነው፤ የወር ገቢዬ ብር 600.00(ስድስት መቶ) ነው፤

ትዳርና ልጅም የለኝም በማለት አመለከተች።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ሁሉም ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 690(1)/በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል እና አንደኛ ተከሳሽ በሁለተኛው ክስ ጥፋተኛ የተባለችበት በ 1996 ዓ.ም 605(ሀ) /የግል ቤቶችን ወይም የተከለከሉ ቦታዎችን መድፈር ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የንብረት ላይ ጉዳቱም ሆነ የተከለከሉ ወይም የግል ቤቶችን መድፈር ወንጀል አፈፃፀሙ ሲታይ የመኖሪያ ቤቶች መድፈር ወንጀሉ ገና ውጤት ያላገኘ እና በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ፤ የተፈፀመውም ሰዎች በተሰበሰቡት በቀን ስለሆነ፤ በንብረት ላይ የደረሰው ጉዳትም መጠኑ ዝቅተኛ ስለሆነ የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 690(1) ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና በመቀጮ ያስቀጣል። በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 605(ሀ) ደግሞ ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ያስቀጣል።

ከዚህ በላይ በተመለከተው የቅጣት ደረጃ መሰረት እርከኑን ለመወሰን እያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌን ለአራት እኩል በማካፈል ደረጃው በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ለተባለው ወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ለተባለው የሚመጣው ስሌት ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት ሲሆን ለመኖሪያ ቤት መድፈር ወንጀሉ ደግሞ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ፅኑ እስራት ይሆናል። በዚህ መሰረት ሁሉም ተከሳሾች በንብረት ላይ ላደረሱት ወንጀል መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሲሆን፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ለፈፀመችው የመኖሪያ ቤት መድፈር ወንጀል ደግሞ አንድ ዓመት ከሦስት ወር እስራት መነሻ ቅጣት ነው። ይህ አንድ ዓመት ከሦስት ወር በአባሪ 1 እርከን 7 ውስጥ የሚወድቅ ስለሆነ፤ ይህ የተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ውጤት ያላገኘና ሙከራ ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 20 መሰረት በ 2 እርከን የሚቀንስ ስለሆነ፤ በዚሁ መሰረትም እርከን 5 ላይ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ተከሳሽ የምትቀጣ ይሆናል። ይህ ፍቅድ ስልጣንም ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ስምንት ወርን መነሻ ቅጣት በማድረግ ወስኗል። አንደኛ ተከሳሽ ተደራራቢ ጥፋት ስለፈፀመች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 184(1)(ለ) መሰረት የሁለቱ ቅጣት ድምር ሁለት ዓመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ 1 መሰረት በእርከን 11 ላይ የተመለከተ ስለሆነ የእርከን 11 ደግሞ ፍቅድ ስልጣኑ ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር እስከ ሁለት ዓመት ከሁለት ወር ነው። ከሁለተኛ እስከ ሰባተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመለከቱትን ተከሳሾች በተመለከተ በአንድ ድርጊት ብቻ ጥፋተኛ የተባሉ ስለሆነና ከላይ አንድ ዓመት ከስድስት ወር መነሻ ቅጣት ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ 1 ላይ በእርከን 9 ላይ የተመለከተ ሲሆን ፍቅድ ስልጣኑም ከአንድ ዓመት ከአራት ወር እስከ አንድ ዓመት ከስምንት ወር በሚደርስ ፅኑ እስራት ነው። የገንዘብ መቀጫውን በተመለከተ ሁሉም ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 69091) የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ስለተባለ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት ከብር አስር እስከ ብር ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር ባለው ፍቅድ ስልጣን መሰረት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወሰን በመሆኑ ከተከሳሾች የገቢ ምንጭ ዝቅተኝነት አንፃር እያንዳንዳቸው በብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1) (መ) መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የተመለከተውን እርከን በአንድ ከፍ ሲያደርገው ከሁለተኛ እስከ ሰባተኛ ያሉትን ተከሳሾች በተመለከተ እርከኑ ወደ 10 ከፍ የሚል ሲሆን አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ ደግሞ እርከኑ ወደ 12 ከፍ ይላል።

ተከሳሾችም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ ያላቀረቡ በመሆኑ የቅጣቱን እርከን ፍ/ቤቱ ዝቅ አላደረውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ከሁለተኛ እስከ ሰባተኛ ያሉ ተከሳሾችን በተመለከተ ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 10 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ከአስር

ወር ስለሆነ እያንዳንዳቸው ተከሳሾች ከፈፀሙት የወንጀል ድርጊት አንፃር በአንድ ዓመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት፤ አንደኛ ተከሳሽ ደግሞ በእርከን 12 ላይ በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት በሁለት ዓመት ከአራት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

ትዕዛዝ

1 ኛ. 5 ኛ እና 6 ኛ ተከሳሾቹ ዕድሜያቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፤ ፍ/ቤቱ በችሎት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸው ወደፊት አመላቸው ይታረማሉ ብሎ ስለገመተ በእነሱ ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ ታግዷል።

2 ኛ. እነዚህ አምስተኛ እና ስድስተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው ለብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የሚበቃ የመተማመኛ ዋስትና ሲጠሩ ይለቀቁ።

3 ኛ. አምስተኛ እና ስድስተኛ ተከሳሾች ቀደም ሲል ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ለቅጣቱ ዓላማ እንዲውል ታዟል።

4 ኛ. አንደኛ፤ ሁለተኛ፤ ሦስተኛ፤ አራተኛ እና ሰባተኛ ተከሳሾች ቀደም ሲል ለዋስትና ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ለቅጣቱ ዓላማ እንዲውል ታዟል።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።